## የኤጀንሲዉ ራዕይ፤ ተልዕኮና እሴቶች

### ራዕይ

ለዜጎች ኢኮኖሚያውዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት፣ ለህግ የበላይነትና ተጠያቂነት የኩነቶች ምዝገባ መረጃ በ2022 በክልላችን አለም አቀፍ ደረጃውን ያሟላና ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ሁኖ ማየት

### ተልዕኮ

- የተገልጋይና ባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ በማሣደግ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የማስመዝገብ ባህልን ማዳበር
- የሰነድ እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አሰራርን በመጠቀም ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ አያያዝና ቅብብሎሽ ስርዓት መዘርጋት
- የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባን በጥራት መፈፀም የሚያስችል ተቋማዊ አቅምንበማሳደግየተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላትን የመረጃ ፍላጎት ማርካት
- ከአጋር አካላት ጋር የቅንጅት እና የትብብር ስራን በማጠናከር የምዝገባ ሽፋንና ጥራትን ማሳደግ
- መረጃዎችን በጥራትበማጠናቀር ለክልሉ ስትራቴጅ አቅጣጫዎች እና ለማህበራዊ አገልግሎት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ
- በጥናትና ምርምር አዳዲስ የአሰራር ስልት በመቀየስየወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓትን ማሻሻል

### እሴቶች

- **የ**መረጃ ደህንነትና ሚስጥርን እንጠብቃለን
- **እ**ውቀትና ክህሎትን ለተጨባጭ ውጤት እንጠቀማለን
- **ቅ**ንጅታዊ አሰራርን እንፈጥራለን
- **ድ**ጋፍና ክትትልን የስራ ማሳለጫ እናደርጋለን
- **ግ**ልፀኝነትና አሣታፊነትን እናረጋግጣለን
- **ብ**ልሹ አሰራርና ኪራይ ሰብሣቢነትን እንፀየፋለን
- **ለ**ደንበኞች እርካታ ቅድሚያ እንሰጣለን
- **ው**ጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎትን እናረጋግጣለን
- **ጤ**ናማና ምቹ የስራ አካባቢ እንፈጥራለን
- **ት**ጉህና ታታሪ እንሆናለን

## የኤጀንሲው ተግባርና ሃላፊነት

በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካች ም/ቤት ጠባቂነት በወጣው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀጽ 5 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ተግባራትን በክልል ደረጃ የሚመራ፣ የሚያስተባበርና የሚደግፍ እንዲሁም የምዝገባ መረጃዎችን አግባብ ላለው የፌደራል አካል የሚያስተላልፍ አግባብ ያለው የክልል አካል በእያንዳንዱ ክልል የሚቋቋም ወይም የሚሰየም ይሆናል በሚል ደንግጓል። ይህንኑ ተግባርና ሃላፊነት ለማስፈጸም መ/ቤታችን የቤጉክመ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በቤጉክመ መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 84/2006 እና በማሻሻያው ደንብ ቁጥር 139/2011 የተቋቋመ ክልላዊ የመንግስት ተቋም ነው። በደንቡ አንቀጽ 7 ለኤጀንሲው የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡-

1. የክብር መዝገብ ሹም በእያንዳንዱ አስተዳዳር ጽህፈት ቤት እንዲመደብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፤
2. በክልሉ ውስጥ በአዋጁ መሠረት ወሳኝ ኩነት በአግባቡ መመዝገቡንና የምስክር ወረቀት መስጠቱን ያረጋግጣል፤
3. ክልሉ የሚያገለግሉ የክብር መዝገቦች ዝግጅትና ሥርጭትን በሚመለከት አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር ይተባበራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ የክብር መዝገቦች ለሁሉም የአስተዳዳር ጽህፈት ቤቶች መሰራጨታቸውን ያረጋግጣል፤
4. የወሳኝ ኩነት የድርጊት መርሐ ግብር እና የመረጃ አጠቃቀም ሥርዓትን አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
5. በክልሉ ውስጥ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አስፈላጊነትን አስመልክቶ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርትና ሥልጠናዎች ይሰጣል ወይም እንደሰጥ ያደርጋል፣
6. የክልሉን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የጥራትና የሽፋን ደረጃ ለመገምገምና ለመቆጣጠር የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፣ በምዝገባ ሂደት በታዩ የአሰራር ችግሮች ላይ የመፍትሔ ሃሳብ ያቀርባል፣
7. በአዋጁ መሠረት የተሰበሰቡ መረጃዎች አግባብ ላለው የፌዴራል አካል ጋር በመተባበር ይሰራል፣
8. ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት አካላት እና አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር በመተባበር ይሰራል፣
9. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይፈጽማል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

10. የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተስማሚ በሆነ ቴክኖሎጂ እየታገዘ የሚሰራበትን ሁኔታ አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር በመሆን ያመቻቻል፣
11. በክልሉ የሚገኙ መንግስታዊ፣ ማህበራዊና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በክልሉ የሚደረገው የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት የተሟላ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣
12. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሳቦችን ወሳኝ ኩነት ምዝገባውን አስመልክቶ አግባብነት ላለው የፌዴራል አካል ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
13. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያግዙ ሌሎች ተዛማች ተግባሮችን ያከናወናል፡፡